# ኮተን ሜድ ኢን አፍሪካ [በአፍሪካ አነስተኛ አርሶአደሮች የተመረተ ጥጥ




ልጆች በምስራቅና ደቡብ አፍሪካ አነስተኛ የጥጥ ማሳዎች ላይ
[የፎቶ አቃፊ/የፎቶ ተረክ] [የፎቶ ፍሬም]

# መቅድም

የኮተን ሜድ ኢን አፍሪካ [በአፍሪካ አነስተኛ አርሶአደሮች የተመረተ ጥጥ ] ዓላማው የበርካታ ጥጥ አምራች አፍሪካውያንን ሕይወት [የኑሮ] ሁኔታ ማሻሻል ነው። ኮተን ሜድ ኢን አፍሪካ ከአጋር የጥጥ ኩባንያዎችና ከCOMPACI [የአፍሪካ ተወዳዳሪ ጥጥ ፕሮጀክት] ጋር በመሆን ቀጣይነት ያለውን [ዘላቂ] የጥጥ አመራረት ማረጋገጥ ይሠራል ። [መርሐ ግብሩ] ሰዎችን፥ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል፤ አከባቢያዊ ጥበቃና ዘለቄታዊ ልማት ታሳቢ የሚያደርግ ፍልስፍና የሚከተል ሲሆን ይኸውም ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና የአካባቢ ጥበቃ መስፈርቶችን የሚያካትት ነው።

ኮተን ሜድ ኢን አፍሪካ በሚከተለው የዘላቂነት መሥፍርት መሠረት በአይ ኤል አ ኮንቬንሽን ቁ 138 እና 182 “አስከፊ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ” ተብለው የተፈረጁት ሥራዎች በሙሉ የተከለከሉ ናቸው። ሆኖም በተለይ በቤተሰብ አነስተኛ ማሳ ላይ ልጆች በምስራቅና ደቡብ አፍሪካ አነስተኛ አ/አደሮች የጥጥ ማሳዎች ላይ [የፎቶ አቃፊ/የፎቶ ተረክ] [የፎቶ ፍሬም] የማይጎዳ ሆኖ የአዋቂዎች ቁጥጥር ያልተለየውና ተገቢ ሥልጠና የተሰጣቸው ሲሆን ነው።

“በምስራቅና በደቡባዊ አፍሪካ ህፃናትና በአነስተኛ ይዞታ ጥጥ የሚያለሙ እርሻዎች ግንኙነት”

ይህ የኮተን ሜድ ኢን አፍሪካ የፎቶ መጽሔት በጥጥ ማምረት ሥራ ውስጥ የተሰማሩ ባለድርሻዎች ሁሉ በተለይም ሥራ ሲበዛባቸው ተጨማሪ [አጋዥ] እጆችን መፈለግ የሚቀናቸው ጥጥ አምራቾችን ለመቀስቀስ [ለማንቃት] የተቀረጸ ነው።

የመጽሔቱ ቅርጽ ከፊት ለፊት ስዕል፥ ከጀርባ ገጽ ጽሑፍ መሆኑ ተጠቀሚው [አሰልጣኙ ወይም የኤክስቴንሽን ሰራተኛው] በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ለአምራቾች ቁልፍ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ያስችለዋል። ስልጠናዎቹ በአሳታፊ መልክ ሊቀርቡ ይገባል።

[ቀጥለው] የቀረቡት ጥያቄና መልሶች ለምስሎቹ እንደ መሪ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

AID BY TRADE FOUNDATION

COTTON MADE IN AFRICA

# የዚህ ፎቶ መጽሔት አጠቃቀም

ይሕ የፎቶ መጽሔት ጠቃሚ [“instructive” = ‘useful and informative’ or instructional? የማስተማሪያ?] መሳሪያ ነው፤ ያካተታቸውንም ምስሎች በስልጠና ወቅት በማሳየት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል [ስልጠናውን ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል] ። የመጽሔቱ አወቃቀር [ቅርጽ] ከፊት ለፊት ስዕል፥ ከጀርባ ገጽ ጽሑፍ መሆኑ ተጠቀሚው [አሰልጣኙ ወይም የኤክስቴንሽን ሰራተኛው] የርዕሰ ጉዳዩን ቁልፍ መልዕክቶች አሳታፊና አጫዋች [አናባቢ/አግባቢ] በሆነ መልኩ ለአምራቾች ለማስተላለፍ ያስችለዋል።

አሰልጣኙ በተሳታፊዎች መካከል አሳብ [ማስተንተን/ማንሸራሸር] እና ውይይትና እንዲፈጥር ይቀሰቅሳል [ያበረታታል]። ግንኙነቱ [ምልልሱ] ለተሳታፊዎች የምር አሳሳቢ በሆኑ [ተሳታፊዎቹን የምር በሚኮነስሩ] ጉዳዩች ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከተሳታፊዎች ጋር የሚደረግ ረዥም [ተከታታይ] የጥያቄና መልስ ቅርጽ ይኖረዋል። የመልዕክቱ [በትክክል] መተላለፍና የነሱም መረዳት ሙሉ በሙሉ የሚረጋገጠው [በሚቀጥለው ገጽ ላይ] በተዘረዘሩት ጥያቄና መልሶች አማካይነት ነው።

በአንድ የስልጠና ክፍለ ጊዜ ውስጥ ምስሎቹ አንድ በአንድ [በየተራ] ለተሳታፊዎቹ [ዕይታ] ይቀርባሉ፤ ተሳታፊዎቹ በምስሉ ላይ የሚታዩትን [የሥራ] እንስቃሴዎች [ትርጉም] እየገለጹ የሚወያዩ [እንዲወያዩ የሚደረግ] ሲሆን የዚህም ዓላማ ተሳታፊዎቹ የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ፋይዳ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። የቀረቡት ዝርዝር ጥያቄና መልሶች ለአሰልጣኙ እንደ መመሪያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ተሳታፊዎቹ የሚሰጥዋቸው መልሶች ወዲያውኑ [ለማስተላለፍ የተፈለገውን] ቁልፉን መልዕክት [አጉልተው] ለማውጣት የማይችሉ ሲሆን ተሳታፊዎቹ ቁልፉን መልዕክት ለማግኘት ይችሉ ዘንድ አሰልጣኙ ተጨማሪ መሪ ጥያቄዎችን ሊያነሳ ይገባል። ጥያቄዎቹም ተዛማጅ መረጃ ለመሰብሰብ በሚያስችል መልኩ ማን/ምን/መቼ/የት/ለምን? በሚሉ ቃላት ሊጀምሩ [የሚጀምሩ ሊሆኑ] ይገባል።

ጥያቄና መልሶቹ ለአሰልጣኙ እንደመመሪያ ሊሆኑ ይገባል እንጂ በስልጠናው ክፍለ ጊዜ ውስጥ መደዳውን ለተሳታፊው ሊነበቡ አይገባም [መነበብ የለባቸውም] ። በአንድ ምስል ላይ ውይይት ከተደረገና ተዛማጅ ጥያቄዎችም ከተነሱ በኋላ ተሳታፊዎች ምስሉ የያዘውን መልዕክት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ [ይቻል ዘንድ] ከመካከላቸው አንዱ እንደገና መልዕክቱን ባጭሩ [ጨምቆ] እንዲያቀርበው ጠይቅ/ቂ። ከዚያ በኋላ ቀጣዩ ምስል ይታይና በዚሁ መልክ ውይይት ይደረግበታል። ተመልካቾች [ተሳታፊዎቹ] ምስሎቹን ለመመልከትና የሚያጭርባቸውን ሃሳብ ለማሰላሰል የሚያስችል ጊዜ መተው ያስፈልጋል [ለመመልከቻና ለማሰቢያ የሚሆን ጊዜ ተውላቸው/ተይላቸው] ። [በተለይ] ጭምቶቹን ሰልጣኞች ለማሳተፍም መትጋት ያስፈልጋል።

እያንዳንዱ ምስል [ለአሰልጣኙ በሚታይ] አንድ [ሌላ] ገጽ የታጀበ ሲሆን ይኸውም [በአማርኛ የተጻፈ] ተራኪ ጽሑፉን [ታሪኩን] እና ጥያቄና መልሶችን፥ እንዲሁም ቁልፉን መልዕክት የያዘ ነው።

ምስሎቹ የሚያሳዩት ታሪክ በሁለት ጥጥ አምራች ቤተሰቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። እባክዎን ለገጸ ባህሪያቱ በአገራችሁ/አካባቢያችሁ የተለመደ ስም በመስጠት ተሳታፊዎች ቅርበት እንዲሰማቸው [በተሳታፊዎችና በታሪኩ መካከል የቅርበት ድባብ እንዲፈጠር] ያድርጉ። እባክዎ በማስታወሻነት ይገለገሉበት ዘንድ ቀጥሎ ያለውን ሰንጠረዥ ይምሉ።

| ምስሉ ላይ በስተግራ በኩል የሚታየው የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች እና ልጆቻቸው ናቸው:: | |
|---|---|
| አባት | |
| እናት | |
| ትልቁ ልጃቸው (15) | |
| ትልቋ ልጅ (13) | |

| ምስሉ ላይ በስተቀኝ የትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ ወላጆች እና ልጆቻቸው ናቸው:: | |
|---|---|
| አባት | |
| እናት | |
| ትልቋ ልጃቸው (14) | |
| ትልቁ ልጅ (10) | |

ይህን የፎቶ መጽሔት ለማሻሻል የሚረዱ ከገበሬዎችና ከአሰልጣኞች የሚሰነዘሩ ሃሳቦችና ለውጦችን በደስታ እንቀበላለን።







ግራ ስዕል 1 ቀኝ

# ስዕል- 1




| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡ በስዕል "ሀ" ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ቤተሰብ ይታየናል። ባለቆርቆሮ ክዳኑ ቤታቸው ጥሩ ሁኔታ ላይ ነው። የሚያርሱባቸው በሬዎች አሏቸው፤ ንፁህና አዳዲስ ልብሶች ለብሰዋል። አምስት ልጆች አሏቸው፤ የመጀመሪያ ልጃቸው ሃያ ዓመቱ ነው [ኑሮውም ሥራውም ከተማ ነው]፥ ሁለተኛው 15 ዓመት፥ ሶስተኛዋ 13፥ አራተኛው 6 ዓመታቸው ሲሆን አምስተኛው [ጨቅላ] ህፃን ነው። ሦስቱ ልጆች የተማሪ ቤት የደንብ ልብስ ለብሰው ይታያሉ።

**ጥ፡ በስዕል 1 በስተቀኝ በኩል ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** የትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ ወላጆች ልጆችና ቤተሰብ ይታዩናል። ደህና የሳር ክዳን ቤት አላቸው፥ በሬ የላቸውም፥ የለበሱትም ንፁህ ያልሆነ ልብስ ነው። አራት ልጆች አሏቸው፤ የ20 ዓመቱ የመጀመሪያ ልጃቸው [ሥራ አጥ ሲሆን ኑሮው ከተማ ነው]፥ ሁለተኛዋ [ዕድሜ 14]፥ ታናሽ ወንድሟ ጨቅላው ዶማ ይዘው የሚታዩት ሁለቱ [ልጆቹ] ተማሪ ቤት አልገቡም፥ ይልቁንም ለሥራ ወደ እርሻ እየሄዱ ነው።

*መልዕክት፡*

*ሁለቱም ቤተሰቦች አጀማመራቸው እኩል ነበር። ሆኖም በስልጠና፥ በትምህርት፥ በገንዘብ አያያዝና ጥሩ የእርሻ ዘዴ በመከተሉ ምክንያት በስዕል ሀ ላይ የሚታየው የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ቤተሰብ የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻል ችለዋል። ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከለው ወላጅ የሚከተለው የእርሻ ዘዴ ህፃናት ማሳ ላይ እንዲሰሩ ግድ የሚልና ለትምህርት የሚሆን ጊዜ የሚያሳጣ ነው። በኮተን ሜድ ኢን አፍሪካ እና በአገራችን ሕግ መሠረት ወላጆች ሁሉንም ልጆች የመማር ዕድል እንዲያገኙና እንዲማሩ ማድረግ አለባቸው።*




ግራ ስዕል 2 ቀኝ

# ስዕል- 2



ግራ ቀኝ

**ጥ፡ በስዕል 2 በስተግራ በኩል ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ ልጆች ወደ ትምሕርት ቤት ሲሄዱ በእጃቸው ምልክት አባታቸውን ይሰናበታሉ።

**ጥ፡ ልጆችን ተማሪ ቤት መሄዳቸው ምን ጥቅም አለው?**

**መ፡** ትምህርት ቤት ውስጥ ህፃናት ማንበብ፥ መጻፍና መቁጠር ይማራሉ። ይህም ብዙ ዕድሎችን ይከፍትላቸዋል። በተጨማሪ ልጆች ወላጆቻቸው የተለያዩ ሰነዶችን እንዲያነቡና ስለ እርሻም የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሊረዷቸው ይችላሉ። የልጆች የሒሳብና የንባብ ችሎታዎች ሲዳብር ወላጆች የእርሻ ሥራውን በተሻለ መልኩ ለማስተዳደር ሊጠቅሙ ይችላሉ። እንዲሁም ህፃናት ወላጆቻቸው ደብዳቤና የውል ሰነዶችን እንዲያነቡ፥ የሰው እንዲሁም የእንስሳትና የሰብል የመድሃኒቶችን ስም መዝግበው እንዲይዙ ሊረዷቸው ይችላሉ።

**ጥ፡ በስዕሉ ላይ በስተቀኝ በኩል ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉስ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉት ወላጆች ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ለሥራ ወደ ማሳው ይሄዳሉ [ሲሄዱ ይታያል]።

**ጥ፡ ህፃናትን ትምህርት ቤት በመላክ ፋንታ ወደ እርሻ መውሰድ ከሚያስከትላቸው ችግሮች ጥቂቶቹ ምን ምንድናቸው?**

*መ፡ ህፃናት ማንበብና መጻፍ እንዳያውቁ ይከለክላል፤ የቤተሰቡ የአስተራረስ ልማድ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህም የሚሆንበት ምክንያቱ ብዙውን ጊዜ ከቤተሰቡ አባላት መካከል እርሻ ነክ ሰነዶችን የሚያነብና በሽያጭ ወቅትም ሒሳቡን የሚያሰላ ሰው አለመኖሩ ነው።*

*መልዕክት፡*

*ትምህርት ቤት መግባት ልጆች ሲያድጉ የተሻለ ዕድል እንዲገጥማቸው ያደርጋል፡፡*




ግራ ስዕል 3 ቀኝ

# ስዕል- 3



ግራ ቀኝ

**ጥ፡ በስዕል 3 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ጠዋት ነው። ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው አባታቸው ሲቆፍር ይታያል። እናታቸው ፍግ ከከረጢት አውጥታ ትበትናለች/ታዳርሳለች/ማሳው ላይ ትጨምራለች]።

**ጥ፡ ወላጆቹ የተፈጥሮ ማዳበርያውን ለምን እየተጠቀሙበት ነው?**

**መ፡** የማሳውን ለምነት ለማሳደግ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ በሚያርስበት ጊዜ የተፈጥሮ ማዳበርያውን ማሳው ላይ ነስንሶ ከአፈሩ ጋር ይቀላቅለዋል። ፍግ የመሬትን ለምነት ለማዳበር በጣም ጥሩና ብዙ ወጪ የማይጠይቅ [ርካሹ] ዘዴ ነው። ፍግ ለማዘጋጀት የሚጠይቀው ወጪ ማዳበሪያ ልግዛ ቢል ከሚያወጣው ያነሰ ነው፤ ምክንያቱም ብስባሽ [እዳሪ] በነፃ የሚገኝ በመሆኑ ነው።

**ጥ፡ ልጆቹም እንደ ወላጆቻቸው ማሳው ላይ በዚህ ስራ ላይ የማይሳተፉት ለምንድን ነው?**

**መ፡** ምክንያቱም ሥራው ረዥም ጊዜ የሚወስድና አስቸጋሪ ሲሆን በአዋቂዎች ብቻ የሚሰራ በመሆኑ ነው። በትምህርት ቀን ህፃናት ልጆች ት/ቤት መሄድ ስላለባቸው ጭምር ነው።




ግራ ስዕል 4 ቀኝ

# ስዕል- 4



| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡ በስዕል 4 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ጥጡ ተተክሎ በማደግ ላይ ነው፤ ጥጡ ባለበት የዕድገት ደረጃ ማሳሳት ያስፈልገዋል። በዚህ ሥራ ላይ ሁሉም የቤተሰቡ አባላት ተሳታፊ ሆነዋል [ሲሳተፉ ይታያሉ]።

**ጥ፡ ህፃናት ይህን ሥራ ሊያግዙ ይችላሉ [ይገባል]?**

**መ፡** ማሳሳት ከባድና አደገኛ ሥራ አይደለም። ህፃናት በእረፍት ጊዜያቸው፥ ከትምህርት ሰዓት ውጭ ወይም ቅዳሜና እሁድ ወላጆቻቸውን በሥራ ሊያግዙ የሚችሉበት ዓይነት ሥራ ነው። ትላልቆቹ ልጆች ደግሞ እንስሶች ወደ ማሳው እንዳይገቡ ሊጠብቁ ይችላሉ።




ግራ ስዕል 5 ቀኝ

# ስዕል- 5



ግራ ቀኝ

**ጥ፡ በስዕል 5 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ ጸረ ተባይ መድሃኒቱን ማሳው ላይ ለመርጨት መድሃኒቱን በውሃ እየበጠበጠ [እያዘጋጀ] ነው። የመከላከያ አልባሳቱን ለብሷል፤ ሙሉ ልብሱን፥ ጫማ፥ ቆብ፥ ጎግል፥ ጓንትና እንዲሁም መድሃኒቱን ከአየር ጋር ወደ ውስጥ እንዳይስበው የሚከላከል ጭምብል አጥልቋል። ከግር እስከራስ የሚለበስ ባይኖር ረዥም ሱሪና እጅጌ ሙሉ ሸሚዝ አነስተኛ ደረጃ ጥበቃ ሊሰጡ ይችላሉ።

**ጥ፡ የመከላከያ አልባሳቱን ለምን ይለብሳል?**

**መ፡** ፀረ ተባይ መድኃኒቶች [በተለይ በውሃ ያልተበረዙ] ጤና ላይ በጣም ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። አዋቂዎች ብቻ በልዩ ጥንቃቄ ሊይዟቸው ይገባል።

**ጥ፡ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ ባዶዎቹን የተባይ መድኃኒት መያዣዎች ምን እያደረጋቸው ነው?**

**መ፡** ኬሚካል የመጣባቸው ባዶ ዕቃዎች ህፃናት አግኝተው እንዳይጫወቱበት ወይም መጠጫ እንዳያደርጉት ወዲያውኑ ሊቀብረው ነው። የጸረ ተባይ መድኃኒት መያዣ የነበረን ባዶ ጠርሙስ ለሌላ ሥራ መጠቀም አይቻልም [አይገባም]። በሰው ጤንነት ላይ ጉዳት ስለሚያስከትሉ፡፡

**ጥ፡ ልጆቹ በዚህ ሥራ ላይ ወላጆችን እንዲያግዙ ይፈቀድላቸዋል?**

**መ፡** የለም፥ አይፈቀድላቸውም። ህፃናትና ልጆች እድገታቸውን ያልጨረሱ እንደመሆናቸው ጸረ ተባይ መድኃኒቶች በተለይ በነሱ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ ነው። ገና 18 ዓመት ያልሞላው ልጅ ውሃ ቢያቀብልም ወደ ኬሚካል መለወስ፤መጨመር፤መርጨት ስራ ማከናወን አይገባውም፡፡ አባትየውም ልጁ ከአካባቢው እንዲርቅ ትዕዛዝ ሲሰጠው ይታያል፡፡ የጸረ ተባይ መድኃኒት መጨመር [የመርጨት ሥራ] ለሚያጠቡና ለእርጉዝ ሴቶችም ፈጽሞ የተከለከለ ነው።




ግራ ስዕል 6 ቀኝ

# ስዕል- 6



ግራ ቀኝ

**ጥ፡ በስዕል 6 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ የጸረ ተባይ/ዐረም መድኃኒት የመርጨቱን ሥራ ጨርሶ ከመስኩ [ማሳው] ተነስቶ ሄዷል። ባዶዎቹን የጸረ ተባይ መድኃኒት መያዣ ዕቃዎች ጉድጓድ ውስጥ ቀብሯል። የመርጫ ዕቃዎቹን ከቤተሰቡ ማሳ ራቅ ብሎ ከተሰራ፥ በቂ ነፋስ ካለውና ዙርያውን ከታጠረ፥ በጠንካራ በርና ቁልፍ በሚዘጋ ቤት ውስጥ እያስቀመጠ ነው።

**ጥ፡ ጸረ ተባይ መድኃኒቱን ቤት ውስጥ አለማስቀመጡ ለምንድን ነው?**

**መ፡** የጸረ ተባይ/ዐረም መድኃኒት ምርቶች በጣም መርዛማ ናቸው። መድኃኒቶቹና የመከላከያ ልብስን ጨምሮ ከነሱ ጋር የተነካካ [ዕቃ] ሁሉ ህፃናት ከማይደርሱበት ጥብቅ ቦታ ሊቀመጡ ይገባል። አባትየውም ራሱንና የተጠቀመባቸውን ቁሳቁስ ሙሉ በሙሉ ማጠብ አለበት።

**ጥ፡ ሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት ምን እያደረጉ ነው?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የምትከተለው ወላጅና ልጆቿ መድኃኒት ከሚረጭበት ማሳ ርቀው ከቤት ቀርተዋል። እናት ምግብ እያዘጋጀች ነው፤ ሴት ልጅ ታግዛታለች። አንደኛው ወንድ ልጅ ዶሮዎቹን ሲመግብ ትንሽየው ወንድማቸው ኳስ ሲጫወት ይታያል። ህፃናት ወላጆቻቸውን በተለያዩ ስራዎች ሊያግዙ ይችላሉ፤ ዶሮዎችን መንከባከብ፥ እንቁላል መሰብሰብ፥ ምግብ ዝግጅት ላይ፥ የጓሮ አትክልት መንከባከብ፥ ልብስ ማጠብ በመሣሠሉ ቀለል ያሉ ሥራዎች።

*መልዕክት፡*

*የጸረ ተባይ ምርቶችና ማሳ ላይ በሚረጩበት ጊዜ የሚደርሱባቸው ዕቃዎች ሁሉ በጣም ጎጂ በመሆናቸው ህፃናት ከማይደርሱበት ቦታ ሊቀመጡ ይገባል። በስዕሉ ላይ የሚታየው ዓይነት ቤት ለመገንባት ካልተቻለ ጸረ ተባይ መድኃኒቶች ቢያንስ በጥብቅ ቦታ ሊቆለፍባቸው ይገባል።*




ግራ ስዕል 7 ቀኝ

# ስዕል- 7



ግራ ቀኝ

**ጥ፡ በስዕል 7 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** በምስሉ ላይ ህፃናት ከቤት ውጪ ወላጆቻቸውን ሊያግዙ የሚችሏቸው አንዳንድ የሥራ ዓይነቶች ይታያሉ። ለምሳሌ [ህፃናት] ከትምህርት ሰዓት ውጪ ከብቶችን ሊያሰማሩ፥ ፀረ ተባይ እና ፀረ-አረም መድኃኒት ከተረጨባቸው ማሳዎች እንዳይገቡ ሊጠብቁ፥ ውሃ ሊቀዱና ማገዶ ሊለቅሙ፥ ፍራፍሬዎችን ሊለቅሙ/ሊሰበስቡ እንዲሁም ከማሳው የተሰበሰቡትን ምርቶች ገበያ ወስደው ሊሸጡ ይችላሉ።

**ጥ፡ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን መታገል ማለት ህፃናት ሰነፎች ይሆናሉ፥ ወላጆቻቸውንም ለማገዝ አይፈቀድላቸውም ማለት ነውን?**

**መ፡** የለም። ህፃናት ጤናቸውንና ዕድገታቸውን ለአደጋ የሚያጋልጡ ሥራዎች ውስጥ ሳይገቡ ለቤተሰቡ ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኙ ይችላሉ። ሆኖም ትምህርት ቤት በመሄድ ተገቢውን ትምህርት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።




ግራ ስዕል 8 ቀኝ

# ስዕል- 8




| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡ በስዕል 8 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ይህ የጥጥ [ለቀማ] ወቅት ነው። ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ጥጥ እየለቀሙ ነው።

**ጥ፡ ልጆቹ ወላጆቻቸውን እያገዙ ነው?**

**መ፡** ከትምህርት መልስ በትርፍ ሰዓቱ ወጣቱ ልጅ ያግዛል፥ እንዳቅሙ። ጥላው ሥር በዕድሜአቸው አነስ ያሉት ወንድና ሴት ልጆች ከጥጡ ውስጥ ያሉትን ባዕድ አካላትን (ቅጠልና ድንጋይ) በማስወገድ ወላጆቻቸውን ያግዛሉ። በእጅ የተለቀመ ጥጥ በማሽን ከሚለቀመው የበለጠ ንጹህ ነው። በጥጥ ውስጥ ያሉ ባዕድ አካላትን በማስወገድ ጥራቱን ማሻሻል ይቻላል። ባዕድ አካላትን ከጥጥ መለየት ህፃናት ሊሰሩት የሚችሉት የሥራ አይነት ነው።

***መልዕክት፡***

*ልጆች በእረፍት ጊዜ፥ ቅዳሜና እሁድ ወይም ከትምህርት ሰዓት ውጪ ጥጥ ለቀማ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፤ ሆኖም በማስፈራራትና በማስገደድ መሆን የለበትም።*




ግራ ስዕል 9 ቀኝ

# ስዕል- 9



| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡ በስዕል 9 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** በስተግራ በኩል የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች፥ በስተቀኝ በኩል የትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ ወላጆች ልጆች ማሳዎች ይታዩናል። የትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ ወላጆች ልጆች ልጆች አብረውት ሲሰሩ ብዙ ጊዜ ቢፈጁም የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ምርት ከትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ ወላጆች ልጆች ምርት በጣም የተሻለ ነው።

**ጥ፡ የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ልጆች ትምህርት ላይ እንጂ ማሳ ላይ ሲሰሩ ካልነበረ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ጥሩ ምርት እንዴት ሊያገኝ ቻለ?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ጥሩ ምርት ሊያፍስ የቻለው ፍግ [ብስባሽ] በመጨመር የአፈሩን ለምነት በማሻሻሉና ጸረ ተባዩንም አስፈገላጊ ሲሆን ብቻ በሰብሉ ላይ በመርጨቱ ነው። በዚህ መንገድ በርካታ ገንዘብ ከማውጣት ድኗል። ልጆቹ አልሰነፉም፤ ትምህርት ቤት ውስጥም ጊዜያቸውንም አላባከኑም። ይልቁንም ለወላጆቻቸው ጠቀሚ የሆኑ በርካታ ነገሮችን ተምርዋል። ለምሳሌ መድኃኒት አጠቃቀምን የሚመለከት መረጃ ወይም ከመስክ ባለሙያው የሚሰጡ መመርያዎችን ሊያነቡ ይችላሉ።

**ጥ፡ በትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ ልጆች ማሳ ላይ የተፈጠረው ችግር [የተበላሸው] ምንድነው?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ የአፈር ምርታማነት የሚያዳብሩ ዘዴዎችን አልተጠቀመም። የጸረ ተባይ መድኃኒት ግዢ ላይ ብዙ ገንዘብ አውጥቷል፥ ሆኖም መድኃኒቱን የጨመረው በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጊዜያት ብቻ አልነበረም። ስለሆነም ተባዮች ሰብሉን አጥፍተውበት ምርቱ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል።
ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ ማንበብና መጻፍ ስለማይችል የተሰጡትን ስልጠናዎች ለመከታተል አልቻለም፤ ልጆቹም ሊረዱት አልቻሉም። የትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ ቤተሰብ እድገት ለማሳየት ዕድሉን ሳያገኝ ቀርቷል።

*መልዕክት፡*

*ትምህርት ቤት የገቡ ህፃናት አይሰንፉም። ይልቁንም ለዕድገት የሚጠቅም የተሻለ አስተዋጽኦ በማበርከት ቤተሰቡንም የበለጠ ትርፋማ ያደርጋሉ።*




ግራ　　　　ስዕል 10　　　　ቀኝ

# ስዕል- 10



ግራ ቀኝ

**ጥ፡ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ ምን እያደረገ ነው? በስዕል10 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** የቤቴሰብ መሪ/አባት/ የጥጥ ምርቱን ለጥጥ ማህበር/ገዢ እየሸጠ ሲሆን ሰራተኞች በጥጥ የተጠቀጠቀ ኬሻዎችን መኪና ላይ እየጫኑ ነው። ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተለው ወላጅ ወደ ገበያው የመጣው ለማገዝም ጭምር ነው።

**ጥ፡ ልጆቹሳ ምን እያደረጉ ነው?**

**መ፡** እነሱ ካባታቸው ጋር [የሚሰራውን] ለመመልከት፣ ሒሳብ ለማስላት፣ የውል ሰነድ በማንበብ በስራው ሲሳተፉ ህፃኑ ልጅ ኳስ ሲጫወት ይታያል።

**ጥ፡ ህፃናት ጥጥ የተሞሉ ኬሻዎችን ሊሸከሙ ይገባል?**

**መ፡** የለም። ለዕድገታቸውና ለጤናቸው ጎጂ ሊሆን ስለሚችል ከባድ ሸክም መሸከም ለህፃናት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

***መልዕክት፡***

*የጥጥ ሽያጭ ወቅት ለአርሶአደሩና ለመላው ቤተሰብ ጠቃሚ ወቅት ነው። ጥሩ የጥጥ ምርትና የተመጠነ የግብአት አጠቃቀም ለቤተሰቡ ለዓመት የሚበቃ ጥሩ ገቢ ሊያስገኝ ይችላል።*




ግራ ስዕል 11 ቀኝ

# ስዕል- 11




| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆችና ቤተሰቡ ምን እያደረጉ ነው?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆችና ቤተሰቡ እየተዝናኑ ነው፤ የዓመቱን የጥጥ ምርት ሒሳብ ይመለከታሉ። ጎረቤታቸው ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ ወላጆች ልጆች ራሱ ማንበብ ስለማይችል የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ልጅ አንድ ጠቃሚ ሰነድ ታነብለት እንደሆን ሊጠይቅ መምጣቱ ነው።

ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች አንዳንዴ ወላጆች ሊያገኙት የማይቻላቸው ዕውቀት ያገኛሉ። በተጨማሪ የውል ሰነዶ ችን፥ መለያ ምልክቶችን፥ ማስታወቂያዎችን፥ መድኃኒቶች ከጥቅም ውጭ የሚሆኑበትን ጊዜና ምርት ነክ መረጃ የያዙ ወ ረቀቶችን ሊያነቡ ይችላሉ።

**ጥ፡ ትምህርት ቤት በመሄድ የተማሩ ህፃናት ምን ይሆናሉ?**

**መ፡** በትምህርት ቤት በኩል በሚተላለፍላቸው ዕውቀት አማካይነት ህፃናት የወላጆቻቸው ኑሮ እንዲሻሻል ሊረዱ ይችላሉ። በተጨማሪ ህፃናት ተሰጥኦቸውን/ችሎታቸውን ለማዳበር የሚችሉ ሲሆን በርትተው ከተማሩም አስተማሪ፥ አዋላጅ፥ መሃንዲስ፥ የሒሳብና የግብርና ባለሙያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።




ግራ

ስዕል 12

ቀኝ

# ስዕል- 12




| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡** **በስዕል 12 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** ትምህርት የሚጀመርበት ት/ቤት የሚከፈትበት ወቅት ነው። ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተሉ የነበሩ ወላጆች ልጆች ከስህተታቸው በመማር ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እየላኩ ነው፡፡ ወደ ት/ቤት በመምጣታቸውም የትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች ልጆች ደስ ብሏቸዋል።

**ጥ፡** **ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ ሃሳቡን ለውጠ ሁሉቱን ልጆቹን ትምህርት ቤት የሰደደበት ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**መ፡** ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ ዓመቱን ሙሉ ትክክለኛ አስተዳደግ የሚከተሉ ልጅና ቤተሰቡን ሲመለከት ነበር። ትምህርት ለህፃናቱና ለመላው ቤተሰብ የተሻለ ዕድል እንደሚፈጥር ተረድቶታል [ተገንዝቧል]፤ ጤንነት፥ ደህንነት፥ ከፍተኛ የሰብል ምርትና የበለጠ ገቢ። ትክክለኛ አስተዳደግ የማይከተለው ወላጅ  ልጆቹን ተማሪ ቤት በመስደድ ራሱንና ልጆቹን ለመጥቀም ወስኗል።




ግራ ስዕል 13 ቀኝ

# ስዕል- 13



| ግራ | ቀኝ |
|---|---|

**ጥ፡** **በስዕል 13 ላይ ምን ይታያቹሃል? ከስዕሉ ምን መገንዘብ/መረዳት ይቻላል?**

**መ፡** የሳምንቱ መጨረሻ ነው፤ ትምህርት የለም። የሁለቱም ቤተሰብ ልጆች እየተጫወቱና እየተዝናኑ ነው።

**ጥ፡** **እንዲህ ማድረግ ለህፃናት ምን ጥቅም ይሰጣል?**

**መ፡** መ፡ህፃናት የመጫወት መብት አላቸው። በተጨማሪ ጨዋታ ለጤናቸውና ለትክክለኛ አስተዳደግ ቁልፍ ነው [በጣም ያስፈልጋል]።

# Aid by Trade Foundation

AbTF (ኤድ ባይ ትሬድ ፋውንድሽን) እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም በጀርመን ሐምበርግ ከተማ በታዋቂው ኢንተርፕረነር የኦቶ ግሩፕ ባለቤት በሆኑት በዶ/ር ሚካኤል ኦቶ የተቋቋመ ግብረሰናይ ፋውንዴሽን ነው፡፡
የፋውንዴሽኑ አላማ ሰዎች ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ ማገዝና ራሳቸውን በዘላቂነት መደገፍ እንዲችሉ መርዳት ነው፡
፡ የፋውንዴሽኑ መርሕም የአካባቢ ደህንነትና የመጪው ትውልድ የኑሮ ዋስትና በሚያስጠብቅ መልኩ ሰዎች ራሳቸውን እንዲረዱ ማስቻል ነው፡፡
AbTF በሥሩ በአፍሪካ አነስተኛ አርሶ አደሮች የሚመረት ጥጥ (Cotton made in Africa) ያስተዳድራል፡፡ የሰዎች እራሳቸውን እንዲረዱ ማስቻል የሚለውን መርሕም በCotton made in Africa በኩል ይተገብራል፡


Imprint

© Aid by Trade Foundation
Bramfelder Chaussee 105
22177 Hamburg
Germany
Tel.: +49 (0)40 - 6461 - 7971
Fax: +49 (0)40 - 6461 - 1009
e-Mail: info@abt-foundation.org
www.cottonmadeinafrica.org

Drawings: Donald Grant, 2014
Printed with kind support of Systain Consulting